| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "ፍትሕ ! ፍትሕ ! ፍትሕ !" |
| ደራሲ ፤ | ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽ. ፡ ቤት ። |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቀ.2012-005 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتَاحي

## ፍትሕ ! ፍትሕ ! ፍትሕ !

---

የጀርመን ፡ "ናስዮናል ፡ ሶስያሊስት ፡ ፓርቲ" ፡ ወይም ፡ ባጪሩ ፡ "ናዚ ፡ ፓርቲ" ፡ በተቋቋመ ፡ ልክ ፡ በ 100 ኛ ፡ ዓመቱ ፥ ሠኔ ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ፥ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በናዚ ፡ ፋሺስት ፡ ጎሲኛ ፡ ወይም ፡ "አይዲዮሎጂ" ፡ በተመሩ ፡ "ውልደተኞች" ፡ ዐመፃ ፡ ስትናወጥ ፡ ከርማለች ። የምልክዮሽን ፡ ወይም ፡ የ"ኢምፔሪያሊዝም"ን ፡ የንጥቂያና ፡ ሀገርን ፡ የማፈራረስ ፡ ርኩስ ፡ ዐላማ ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ለማስፈጸም ፥ ከስድሳ ፡ ባላነሱ ፡ የሽዋ ፡ የዐሩሲ ፡ የባሌ ፡ የሐረርጌ ፡ የከፋ ፡ የወለጋ ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፡ ወረዳዎች ፥ ቊጥራቸው ፡ በውል ፡ ያልታወቀ ፡ በመቶ ፡ ምናልባትም ፡ በሺሕ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ንጹሓን ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ጭዳ ፡ ተብለዋል ፤ ቤት ፡ ንብረታቸውም ፡ ወድሟል ።

ፍትሕ ፡ የሰላም ፡ መሠረት ፡ ነውና ፥ ይህን ፡ ፀረ ፡ ሀገር ፣ ፀረ ፡ ሥልጣኔ ፡ ድርጊት ፡ ዐቅደው ፡ የፈጸሙና ፡ ያስፈጸሙ ፡ ወንጀለኞች ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሀገር ፡ ክዳት ፡ አንቀጽና ፡ በነፍስ ፡ ማጥፋት ፡ አንቀጽ ፡ ተከሰው ፡ ፍርዳቸውን ፡ ማግኘት ፡ ይኖርባቸዋል ። ለዚህም ፥ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ ተፈጽሞ ፡ የነበረ ፡ በደል ፡ በደርግ ፡ ውንብድና ፡ ተድበስብሶ ፡ ፍርድን ፡ ሳያገኝ ፡ እንደቀረ ፡ ኹሉ ፥ ደርግ ፡ ዐሥር ፡ ዕጥፍ ፡ ያባባሰውን ፡ በደል ፥ እንዲሁ ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፡ አድበስብሶት ፡ ተራውን ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ በደል ፡ አክሎበት ፥ ዛሬ ፡ ዳግም ፡ ተድበስብሶ ፡ እንዳይቀር ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ፈጥኖ ፡ እግዚእናውን ፡ በማስከበር ፥ በሀገራዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱና ፡ በራሱ ፡ ፈታሒ ፡ ሥልጣን ፡ ትክክለኛውን ፡ ፍርድ ፡ በከሓድያን ፡ ላይ ፡ ማስፈጸም ፡ ይጠበቅበታል ።

*«ወንጀለኞች ፡ በዘር ፡ ማጥፋት ፡ ወንጀል ፡ ለዓለም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቅረቡ»* ፡ ለሚለው ፡ ለባዕዳን ፡ የማዘናጊያ ፡ ተንኰል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዦሮውን ፡ ሊሰጥ ፡ አይገባውም ። ይህኛው ፡ አካኼድ ፥ በባዕድ ፡ ሠራሹ ፡ የአፓርትሀይድ ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ የተፈጠረው ፡ መሠረታዊው ፡ የሀገሪቱ ፡ ችግር ፡ ለመቼውም ፡ እንዳይፈታ ፡ ከማድረጉ ፡ ሌላ ፥ ሀገሪቱ ፡ ወደታቀደባት ፡ ጥፋት ፡ በተረጋገጠ ፡ እንድታመራም ፡ ያደርጋታልና ፥ አጥብቀን ፡ እንቃወመዋለን ። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ከነሕገ ፡ ውንብድናው ፡ መወገድ ፡ አለበት ፤ ከሓድያንና ፡ ወንጀለኞችም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዳኘት ፡ አለባቸው ። የኢትዮጵያ ፡ እግዚእና ፡ ይህን ፡ ያስገድዳል ።

ከሩቅ ፡ ኾነው ፥ ለምልክዮሽ ፡ ዐላማ ፡ ይህን ፡ ጥፋት ፡ የፀነሱና ፡ ያስፈጸሙ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎችም ፥ *«ተከናንበው ፡ ቢተኙ ፡ ገልጦ ፡ የሚወጋ ፡ አምላክ ፡ አለና»* ፥ የማይተኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ ይፋረዳቸዋል ።

በ"ዘር ፡ ማጽዳት" ፡ ሽፋን ፡ ሀገራዊነትን ፡ የማጥፋት ፡ ዘመቻ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ እንሆ ፡ ተካኺዷል ። ኢትዮጵያ ፡ ቀዳሚት ፡ ሀገር ፡ ናት ፤ ሀገር ፡ ማለትም ፥ በርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፥ በሀገራውያንና ፡ በሰፈሩበት ፡ ምድራቸው ፡ መዋሐድ ፡ የሚከወን ፡ ኹነት [1] ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ ማለት ፡ ነው ። የኢትዮጵያን ፡ ኹነት ፡ ለማፈራረስ ፡ ይህን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐም ፡ ሐራ ፡ አስቀድሞ ፡ ማጥፋት ፡ ስለሚያስፈልግ ፥ የምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፥ በደም ፡ በታጠቡ ፡ ምንደኞቻቸው ፡ አማካይነት ፥ ዛሬም ፡ ጥፋታቸውን ፡ በማይበርድ ፡ እልክ ፡ ቀጥለዋል ። ዛሬም ፡ ግን ፡ ያልደረሱበት ፡ ነገር ፡ አለ ፦ *ርትዓዊ ፡ ኹነት ፡ ይሰፋል ፡ ይጠባል ፡ እንጂ* ፥ *አይፈርስም !* ኢትዮጵያም ፡ በሥልጣኔዋ ፡ ርቱዕነት ፡ ሌሎች ፡ ሀገሮችን ፡ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንገድ ፡ እያዋሐደች ፡ ትሰፋለች ፡ እንጂ ፥ በምልከኞች ፡ ተንኰል ፡ ፈራርሳ ፡ በውጥን ፡ ቅጥ ፡ ተዳብሎ ፡ ወይም ፡ "ኮንፌደሬሽን" ፡ አትጨፈለቅም ።

ምላስ ፡ ጠንቅ ፡ ኾኖባቸው ፥ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.- ብልጽግና ፡ ፓርቲ ፡ የ"አሮሞ ፡ ውልደተኞች" ፡ በዝርዝርና ፡ በይፋ ፡ እንደነገሩን ፥ ቀደም ፡ ሲል ፡ ደግሞ ፥ የበላያቸው ፡ በዐምባ ፡ ገነን ፡ "ውሳኔ" ፡ እንዳረጋገጡልን ፥ በሀገራዊው ፡ ቋንቋ ፡ በዐማርኛም ፡ ላይ ፡ ተዘምቷል ።

በዚህም ፡ አላበቃ ፤ *«ዶሮን ፡ ሲደልሏት ፥ በመጫኛ ፡ ጣሏት»* ፡ እንዲሉ ፥ ዐምባ ፡ ገነኑ ፡ አገዛዝ ፡

---

1 ኹነት ፤ ወይም ፡ በግእዝ ፡ ኩነት ፥ የአካል ፡ ህላዌ ፤ መንግሥት ፡ (State) ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

ለዕርድ ፡ ያዘጋጀውን ፡ የዐዲስ ፡ አበባን ፡ ሥልጡን ፡ ሕዝብ ፥ በዐረብ ፡ ገንዘብና ፡ በቻይና ፡ ምህንድስና ፡ የተሠሩ ፡ ያንድ ፡ ሰሞን ፡ ብርቃብርቆችን ፡ እያቀለጨለጨለት ፡ ሊያዘናጋውም ፡ ሞክሯል ። ሞኙ ፡ ሆይ! ተላሌ ፡ ሆይ! በዚህ ፡ ዐይነት ፡ አካኼድ ፡ መቼም ፡ ቢኾን ፡ አትደርስበትምና ፥ ሌላ ፡ ጥፋት ፡ ሳትፈጽም ፡ በፊት ፡ እንንገርኽ ፦ እያንዳንዱ ፡ ኦሮሞ ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነቱ ፡ ከሌሎች ፡ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራውያን ፡ ጋራ ፡ ሀገረ ፡ ኵሽ ፡ ኢትዮጵያን ፥ ገና ፡ በጧቱ ፡ በመሠረቱ ፥ መሥርቷል ፤ ሌላ ፡ ሀገር ፡ የለችውም ።

ከ 72% ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ (ወይም ፡ 80 ፡ ሚልዮን) ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ተከታዮች ፡ በኾኑባት ፡ ሀገር ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ በገዛ ፡ ሀገራቸው ፡ ተወግደውና ፡ ተጨቍነው ፡ ይኖራሉ ፧ እስከ ፡ መቼስ ፡ የተዋሕዶ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሲቃጠሉ ፣ ካህናትና ፡ ምእምናን ፡ ሲታረዱ ፡ ይኖራሉ ፧

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የዥመረውን ፡ ፍትሕ ፡ እግዚአብሔር ፡ በ 2013 ፡ ዓ.ም. ፡ እንዲፈጽምለት ፡ እንለምነዋለን ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ኢ. ሀ ሥ አ

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

**ሥልጡንሕዝብና ።**
**www.slttunhzb.net**


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ።